# የ7ኛ ክፍል
# ሙዚቃ ሲለበስ

# መ ግ ቢ ያ

ይህ የሙዚቃ ሲለበስ በአጠቃላይ 16 ክፍለ ጊዜ ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ሴሚስተር 8 ክፍለ ጊዜ እንዲኖረው ሆኖ ተዘጋጅቷል።

ሲለበሱ የኘሮጀክት መርህ መማርን ( Project – Based Learning ) መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ ከዚህ አንፃር ሲለበሱ ወስጥ የሚከተሉትን መርሆዎች ለማካተት ተሞክሯል።

- ከተግባር ጋር የተያያዙ የመማር ስልቶች ፣
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲማሩ ዕድል መስጠት፣
- ተማሪዎች ለመማር ራሳቸው ኃላፊነት የሚወስዱበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ማድረግ፣
- ኘሮጀክቶች ትርጉም ያለው መማርንና ከተማሪዎች ቀደሞ ልምድ ጋር የተገናዘቡ መሆናቸው፣
- የመማር ማስተማሩ ሂደቱና ኘሮጀክቶች በተማሪዎች እንዲገመገሙ መደረጉ፣
- እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን ሥራ እንዲገመግም የሚያበረታታ መሆኑ፣
- ተማሪዎች የጠለቀ ግንዛቤ እንዲያገኙ ዕድል መሰጠቱ፣
- መምህሩ ትምህርቱን በማመቻቸትና አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ላይ ማተኮሩ፣

ስለዚህ እነዚህን ዋና ዋና መርሆዎች መሠረት በማድረግ ትምህርቱን መተግበር ከመምህሩ ይጠበቃል።

## ክፍለ ትምህርት 1 ፡ የሙዚቃ ጠቀሜታና ክፍሎች /2 ክፍለ ጊዜ/

- የሙዚቃን ጠቀሜታ ከህብተረሰብ አንፃር በመተንተን ሪፖርት ያቀርባሉ።
- የቃናን ፅንሰ ሀሳብ በመረዳት ድምፅ ከሚያወጡ ከቁሳቁሶች ቀላል ዜማዎችን ይጫወታሉ፡
- የዜማ አደረጃጀትና አይነቶችን በመገንዘብ ከ3-5 የሚደርሱ ዜማዎችን በመምረጥ ይተነትናሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o ሙዚቃ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ጥቂት ሰዎችን በመጠየቅ ይተነትናሉ። | 1.1. የሙዚቃ ጠቀሜታ<br>/1 ክፍለ ጊዜ/ | **ክንዋኔ 1**<br>o ሙዚቃ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ እያንዳንዱ ተማሪ ቢያንስ የ5 ሰዎችን ቃለመጠይቅ አጠናቅረው ሪፖርት ማቅረብ።<br>**ክንዋኔ 2**<br>o በሪፖርቱ ላይ የክፍሉ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ።<br>**ክንዋኔ 3**<br>o ሪፖርቱን ማጠቃለል። |
| o ድምፅ ከሚሰጡ ቁሳቁሶች ከ5 ያላነሱ የተለያዩ ድምጾችን ያወጣሉ።<br>o ድምፅ ከሚያወጡ ቁሳቁሶች | 1.2. ሙዚቃ ክፍሎች /<br>1.2.1.ሪትም<br>1.2.2. ቃና<br>1.2.3. ዜማ /አደረጃጀትና | o ስለ ሙዚቃ ክፍሎች አጠር ያለ ገለፃ ከተደረገላቸው በኋላ ስለሚያከናውኑት ተግባራት ውይይት ማካሄድና ስምምነት ላይ መድረስ ተማሪዎች የሚሰጧቸው |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| በጣም ቀላል ዜማዎችን ይጫወታሉ።<br><br>ከ3-5 የሚደርሱ የተለያዩ ዜማዎችን በመምረጥ የዜማ አደረጃጀታቸውና ዓይነታቸው የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ይተነትናሉ።<br><br>o | አይነቶች/<br><br>/1 ክፍለ ጊዜ/ | ጠቃሚ አስተያየቶችን ማስተናገድ ይገባል።<br>**ክንዋኔ** 1<br>o ከ5 ያላነሱ የተቆራረጡ ብረቶች ወይም እንጨቶች ወይም ድንጋዮች ወይም የተለያየ መጠን ያለው ውሀ የተሞላባቸው ጠርሙሶች/ብርጭቆዎች/ የተለያየ ድምፅ ማውጣት በእነዚህ ቁሳቁሶች ቀላል ዜማዎችን መጫወት።<br>**ክንዋኔ** 2<br>o ሙከራዎችን ለክፍሉ ተማሪዎች ማቅረብና ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡባቸው ማድረግና የተሻለውን እንዲመርጡ ማድረግ።<br>**ክንዋኔ** 3<br>o ከ3-5 የሚደርሱ የተለያዩ ዜማዎች በመምረጥ የዜማ አደረጃጀታቸውንና አይነታቸው የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን በመተንተን ሪፖርት ማቅረብ። |

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች**

- ድምፅ የሚያወጡ በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶች፣
- ካሴቶች ፣ ካሴት ቴኘሪከርደር፣

ክትትልና ግምገማ

- ሙዚቃ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ትንተና ሪፖርት ማዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣
- ያቀረቡትን ሪፖርት በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ድምፅ ከሚሰጡ ቁሳቁሶች የሙዚቃ ድምፅ ማውጣታቸውንና ቀላል ዜማዎችን መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ከ3-5 የሚደርሱ ዜማዎችን በመምረጥ የዜማ አደረጃጀታቸውንና አይነታቸውን መተንተናቸውን ከሪፖርታቸው ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 2፡ የሙዚቃ ኖታዎች ምልክቶችና አጨዋወታቸው / 3 ክ/ጊዜ/

- ቀላል ሪትሞችን/ነጥብ ያላቸውና ነጥብ የሌላቸውን /በጭብጨባና በሪትም የሙዚቃ መሳሪያዎች በመጫወት ያሳያሉ።
- ቀላል የጊዜ አመልካችን ፅንሰ ሀሳብ በመረዳት ቀላል ሪትሞችን ይጫወታሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o ቀላል ሪትሞችን /ነጥብ የሌላቸውን ከእነእረፍት ምልክቶቻቸው በጭብጨባ ወይም በከበሮ በመጫወት ያሳያሉ።<br>o ቀላል ባለነጥብ ኖታዎችን / ከሙሉ እስከ ሩብ/ ለብቻቸውና ነጥብ ከሌላቸው ጋር የተቀላቀሉትን በመጫወት / በጭብጨባ ወይም በከበሮ / ያሳያሉ።<br><br>o የመክፈያ መስመርና የመዝጊያ መስመሮችን አጠቃቀም ያሳያሉ።<br>o በቀላል የጊዜ አመልካቾች የተዘጋጁ ቀላል ሪትሞችን ይጫወታሉ። | 2.1. የተለያዩ የጊዜ ቆይታ ያላቸው ኖታዎች፣<br>/1 ክ/ጊዜ/<br>2.1.1. ነጥብ የሌላቸው ኖታዎች ከእነእረፍት ምልክቶቻቸው ፣<br>o ሙሉ<br>o ግማሽ<br>o አንድ አራተኛ<br>o አንድ ስምንተኛ<br>o አንድ አሥራ ስድስተኛ<br>2.1.2. ባለነጥብ ኖታዎች<br>o ሙሉ<br>o ግማሽ<br>o አንድ አራተኛ<br>2.2. ሪትምና ሜትር | **ክንዋኔ 1**<br>o ከ15 ያላነሱ ቀላል ነጥብ የሌላቸው ኖታዎችን ከእረፍት ምልክቶቻቸው ጋር በማቀላቀል በጭብጨባ ወይም በከበሮ መጫወት።<br><u>ምሳሌ</u>፡ ሀ/<br>ለ/<br>ሐ/<br>መ/<br>ሠ/<br>**ክንዋኔ 2**<br>o የተለማመዱባቸውን /ክንዋኔ 1/ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣ |

| የሚጠበቅ አዋጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | /2 ክ/ጊዜ/<br>2.2.1 የመክፈያ መስመር (Bar line)<br>2.2.2 የመዝጊያ መስመር (Double bar line)<br>2.2.3 አመልካቾች<br>2 ፣ 3 ፣ 4<br>4 4 4 | **ክንዋኔ 3**<br>o ከ10 ያላነሱ ቀላል ባለነጥብ ኖታዎችን ነጥብ ከሌላቸው ጋር በማቀላቀል በማጨብጨብ ወይም በከበሮ መጫወት።<br>**ምሳሌ ፡** ሀ/<br>ለ/<br>ሐ/<br>መ/<br>o በፅንሰ ሀሳቦቹ ላይ መጠነኛ ግንዛቤ ካገኙ በኋላ ክንዋኔውን በቡድን እንዲሰሩ ማድረግ፡<br>**ክንዋኔ 1**<br>o ከ10 የማያንሱ ሪትሞችን ተስማሚውን የጊዜ አመልካች እንዲያመላክቱ ማድረግ፡<br>**ምሳሌ፡** ሀ/<br>**መልስ** 3<br>4<br>**ክንዋኔ 2**<br>o ከ5 የማያንሱ በሁለት ተከፍለው አንድ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | ላይ የሚጫወቷቸው ሪትሞችን በማጨብጨብ ወይም በሙዚቃ መሳሪያ /ከበሮ /መጫወት ፡፡<br>**<u>ምሳሌ</u>** ሀ/<br>ለ/ |

## የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡

- ቀላል የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች /ሪትም ፣ ስቴክ፣ ከበሮ፣ቶንብሎክ/፣

## ክትትልና ግምገማ

- ቀላል ሪትሞችን በትክክል መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የመክፈያ መስመርና፡ የመዝጊያ መስመሮችንና የጊዜ አመልካቾችን ጠቀሜታ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ፣
- ቀላል ሪትሞችን በትክክለኛው የጊዜ አመልካች መሠረት መሥራታቸውን የጽሁፍ ጥያቄዎችን በመስጠት ማረጋገጥ፣፡

## ክፍለ ትምህርት 3 ፡ የሙዚቃ አፃፃፍና አዘማመር /3 ክፍለ ጊዜ/

- የትሬብልና ቤዝ ቁልፎች ፣ ሻርፕና ፍላት አንድነትና ልዩነት፣ እንዲሁም ጠቀሜታ ያስረዳሉ።
- የምልክቶቹን አፃፃፍ ያሳያሉ።
- ቀላል የሙዚቃ ድርሰቶችን ያነባሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o የትሬብልና ቤዝ ቁልፎችን በስታፍ ላይ አስተካክለው በመፃፍ ያሳያሉ።<br>o በትሬብልና ቤዝ ቁልፎች የኖታዎችን ስሞች በስታፍ ላይ ይለያሉ።<br>o ቀላል እሰኮሮችን/የሙዚቃ ድርሰቶች/ ያነባሉ።<br>o የትሬብልና ቤዝ ቁልፎችን ጠቀሜታ ያስረዳሉ።<br>o የሻርፕና ፍላት ጠቀሜታን ይገልፃሉ፡<br>o የሻርፕና ፍላት አፃፃፍ በስታፍ ላይ ያላያሉ። | 3.1. የሙዚቃ ፊደሎችና ምልክቶች /1 ክ/ጊዜ/<br>3.1.1. የትሬብልና ቤዝ ቁልፎች በስታፍ ላይ አቀማመጥ<br>3.1.2. የኖታዎችን ስም በስታፍ ላይ /በትሬብልና በቤዝ ቁልፎች/<br>3.1.3. ሻርፕና ፍላት<br>3.1.4. እስኮሮችን /የሙዚቃ ድርሰቶች/<br>/2 ክ/ጊዜ/ | o ፅንሰ ሀሳቦቹን ማስረዳትና ክንዋኔውን እንዲሰሩ ማድረግ፡<br>**ክንዋኔ 1**<br>o ከ10 የማይበልጡ በስታፍ ላይ የተፃፉ ኖታዎችን ትክክለኛ ስማቸውን ማፃፍ<br>**ክንዋኔ 2**<br>o ከ15 ያልበለጡ ቀላል ዜማዎችን ከእሰኮር ላይ ማንበብ፡<br>**ምሳሌ፤**<br>ሀ/<br>ለ/ |

### የሙዚቃ መሣሪያዎች

- የሙዚቃ ምልክቶችን ፡ የኖታዎችን ስም የሚያሳይ ቻርት፣
- ውድ ያልሆነ ኪቦርድ /ቢያንስ ሁለት አክታቭ ያለው/፣

### ክትትልና ግምገማ

- ምልክቶቹን መፃፋቸውንና የሰሩትን ሥራ በመመልከት ማረጋገጥ፣
- የኖታዎችን ስሞች መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ቀላል እስኮሮችን /የሙዚቃ ድርሰቶችን/ ማንበባቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የምልክቶቹን ጠቀሜታ ማወቃቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 4 ፡ ባህላዊ ዘፈኖች /3 ክፍለ ጊዜ/

- በክልሉ የሚገኙ ከሥራ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችን በመተንተን ሪፖርት ያቀርባሉ፣
- ሁለት ከሥራ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችንና ሁለት በአንቺ ሆዬ ቅኝት የተዘፈኑ ዜማዎችን በመጫወት ያሳያሉ፣

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o በክልሉ የሚገኙ ከሥራ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችን ተንትነው በሪፖርት መልክ ያቀርባሉ።<br>o ቢያንስ ሁለት የሥራ ባህላዊ ዘፈኖች በመጫወት ያሳያሉ።<br>o ቢያንስ ሁለት በአንቺ ሆዬ ቅኝት ሁለት ዜማዎችን በማዜም ያሳያሉ። | 4.1. ከሥራ ጋር የተያያዙ በክልሉ የሚገኙ ባህላዊ ዘፈኖች፣<br>/2 ክ/ጊዜ /<br>4.2. በአንቺ ሆዬ ቅኝት የተዘፈኑ ዜማዎች፣<br>/1 ክ/ጊዜ / | **ክንዋኔ 1**<br>o በክልሉ የሚገኙ ከ2-3 የሚደርሱ ከሥራ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችን ግጥም ፣ አልባሳት ፣ዘፈኖቹን ለማጀብ የሚያገለግሉ የሙዚቃ መሳሪያዎች ፡ አጨዋወት በመዘርዘር በሪፖርት መልክ ማቅረብ፣ሪፖርቱ ለተማሪዎች ቀርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግና የተሻለውን በመምረጥ እንዲጫወቱት ማድረግ፣<br>**ክንዋኔ 2**<br>o የተመረጡትን ባህላዊ ዘፈኖች ተለማምደው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፡ በቀረበው ላይ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣<br>**ክንዋኔ 3** |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | o ከ1-2 የሚደርሱ በአንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝት የተዘፈኑትን ዘፈኖች ግጥም መፃፍና፡ የመረጧቸውን ዘፈኖች በክፍሉ ተማሪዎች ፊት ማዜማና አስተያየት መቀበል። |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች

- ካሴት ፡ ካሴት ቴኘሪከርደር ፣
- ለሥራ ባህላዊ ዘፈኖች የሚያስፈልጉ አልባሳት ፡ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣አስፈላጊ ቁሳቁሶች፣

## ክትትልና ግምገማ

- ባህላዊ ዘፈኖችን መተንተናቸውን ሪፖርታቸውን በመመልከት ማረጋገጥ፣
- ባህላዊ ዘፈኖቹን መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በአንቺ ሆዬ ቅኝት ዜማዎችን መሰብሰባቸውን በሪፖርታቸው ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 5 ፡ መዝሙሮች /3 ክፍለ ጊዜ/

- ከ4 ያላነሱ ለሀገርና ለህብረተሰብ ጠቀሜታ ያላቸውን መዝሙሮች ግጥምና ዜማ ይደርሳሉ፡
- የደረሷቸውን  መዝሙሮችና ሌሎች ታዋቂ ዜማዎችን በመዘመር ያሳያሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o ከልማት ፡ ከዲሞክራሲ መርሆዎችና እሴቶች፣ ከሴቶች እኩልነት፣ ከኤች አይቪ፡ ኤድስ ጋር የተያያዙ ቀላል መዝሙሮችን /ግጥምና ዜማ/ ይደርሳሉ።<br><br>o ከደረሷቸው መዝሙሮች ውስጥ የመረጡትንና ካልደረሷቸው ውስጥ ታዋቂ ዜማዎችን በመዘመር ያሳያሉ። | 5.1. ከልማት፡ ከዲሞክራሲ መርሆዎችና እሴቶች፡ ከሴቶች እኩልነት ፡ ከኤች አይቪ ኤድስ ጋር የተያያዙ መዝሙሮች /3 ክ/ጊዜ/<br><br>5.1.1. ግጥም መድረስ<br>5.1.2. ዜማ መድረስ<br>5.1.3. መዘመር | **ክንዋኔ 1**<br>o በእነዚህ ርዕሶች ላይ ግጥም በጥንድ ሆነው መድረስ ከተደረሱት ውስጥ የተሻለውን መምረጥ፣<br><br>**ክንዋኔ 2**<br>o ለተመረጡት ግጥሞች ዜማ ማውጣት ከወጡት ዜማዎች ውስጥ የተሻለውን መምረጥ፣<br>**ክንዋኔ 3**<br>o ከእነዚህ ርዕሶች ጋር የተያያዙ የሚዜሙ ዜማዎችን በመምረጥ ማዜም። |

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች**

- ካሴት ፣ካሴት ቴኘሪከርደር ፣

**ክትትልና ግምገማ**

- የመዝሙሮቹን ግጥምና ዜማ መድረሳቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- መዝሙሮቹንና የመረጧቸውን ሌሎች ዜማዎች ማዜማቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 6 ፡ የሙዚቃ ታሪክ /3 ክፍለ ጊዜ/

- የክልሉንና ሀገር አቀፍ የጥቂት ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያን ፡ ዘፋኞችና ሙዚቃ አቀናባሪዎችን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች አጠናቅረው ያቀርባሉ።
- ከክልልና ከሀገር አቀፍ የታዋቂ ዘፋኞችን ዜማዎች በማዜም ያሳያሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o ከክልል ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያን ፡ አቀናባሪያንና ዘፋኞች ቢያንስ ከእያንዳንዳቸው የሁለቱን አጠናቅረው ያቀርባሉ፡<br>o ከሀገር አቀፍ የሙዚቃ ደራሲያን ፡ አቀናባሪያንና ዘፋኞች ቢያንስ ከእያንዳንዳቸው የሁለቱን አጠናቅረው ያቀርባሉ።<br>o ከክልልና ከሀገር አቀፍ ቢያንስ ከእያንዳንዳቸው ሶስት የታዋቂ ዘፋኞችን ዜማዎች በማዜም ያሳያሉ። | 6.1. ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች / 1 ክ/ጊዜ/<br>6.1.1. ሀገር አቀፍ /ቅዱስ ያሬድ፡ አሸናፊ ከበደ/<br>6.1.2. ክልል አቀፍ /1 ክ/ጊዜ/<br>6.2. ታዋቂ ዘፋኞችና ሙዚቃ አቀናባሪዎች፡ /1 ክ/ጊዜ/<br>6.2.1. ሀገር አቀፍ /ጥላሁን ገሠሠ ፣ አስቴር አወቀ ፣ቴዎድሮስ ካሳሁን/<br>6.2.2. ክልል አቀፍ | **ክንዋኔ 1**<br>o ከሀገር አቀፍ የሙዚቃ ደራሲያን ቢያንስ የሁለቱን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች በሪፖርት መልክ ማጠናቀር ፡ ሪፖርቱን ለክፍሉ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣ ይህ ክንዋኔ በቡድን ሊሰራ ይችላል።<br>**ክንዋኔ 2**<br>o ከክልሉ ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያን ቢያንስ የሁለቱን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች በሪፖርት መልክ ማጠናቀር፣ ሪፖርቱን ለክፍሉ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ፣ ይህ ክንዋኔ በቡድን ሊሰራ ይችላል። |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | **ክንዋኔ 3**<br>o ከሀገር አቀፍ ታዋቂ ዘፋኞች ቢያንስ የሁለቱን ፡ ከክልል ቢያንስ የአራቱን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች በሪፖርት መልክ ማጠናቀር፡ በሪፖርቱ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ፣<br>**ክንዋኔ 4**<br>o የታዋቂ ዘፋኞችን ዜማዎች ከክልሉ /ቢያንስ ሶስቱን/ ፣ ከሀገር አቀፍ /ቢያንስ ሶስቱን/ በመለማመድ ማዜም፣ የተለማመዱትን ለተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ። |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች

- ካሴት ፣ካሴት ቴፕሪከርደር ፣

## ክትትልና ግምገማ

- የሙዚቃ ደራሲያን ፡ አቀናባሪያንና ዘፋኞች አጠናቅረው ማቅረባቸውን ሪፖርታቸውን በመመልከት /በማንበብ/ ማረጋገጥ፣
- የታዋቂ ዘፋኞችን ዜማዎች ማዜማቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣